# አገር ከጂው ንጉሥ

(ከማህሉ በቀለ)

እማማ ኢትዮጵያ፣ ሞኝ ነሽ ተላላ
የገደለሽ ቀርቶ፣ የሞተልሽ በላ
የሞተልሽ ቀርቶ፣ ገዳይሽ መብላቱ
ልጆችሽን ወግቶ፣ አገር በመክዳቱ።

ያንች ጉድ አያልቅም፣ ዛሬም ታዳያለሽ
ሀብትሽን ቅርስሽን፣ ለነመለስ ሰጥተሽ
ልብና ሆድሽን፣ ክፍትፍት አድርገሽ
ሲንቁሽ ሲሰድቡሽ፣ ቅሌትሽን ችለሽ
አገር ከጂዎቹን፣ እጓዳሽ አስቀምጠሽ
ንፁህ ልጆችሽን፣ እስር ቤት አጉረሽ
ያንችስ ለብቻ ነው፣ በጣም ትገርሚያለሽ።

እነዛ ልጆችሽ፣ እጓዳሽ የገቡ
እንደወፍጮ ቤት በግ፣ በጣም የደለቡ
ሌሎቹ ሲያለቅሱ፣ ሲጎዱ፣ ሲራቡ
ደንታ የሌላችው፣ ምንም የማያስቡ
እስኪ ተጠየቂ፣ ወይዘሮ ኢትዮጵያ
ስለነዚህ ልጆች፣ ስለአንች ዝርያ።

የእናት ሆድ ዥንጉርጉር፣ መሆኑን አውቃለሁ
ጨካኝ ልጆችሽን፣ ምከሪ ብያለሁ
አለበለዚያ ግን፣ እኔ አምርሪያለሁ
አንች ስለጨከንሽ፣ እኔም ጨክኛለሁ
ፋሽስቱ ልጅሽን፣ እታገለዋለሁ
በሰፈረው ቁና፣ እኔም እሰፍረዋለሁ።

መለስ ንጉሥ ሆኖ፣ እጅጉን አስፈሪ
እሱ ዳኛ ሆኖ፣ መርማሪ አሳሪ
እንደ እህል ሲያፍሰው፣ ወጣቱን ተማሪ
አገር ሲያል ሲሆን፣ ለሰርቶ አዳሪ
እሬሳ ተቀባይ፣ ሳይጠፋ ቀባሪ
ስንቱን አውሬ በላው፣ ኢትዮጵያ በይ እሪሪሪ!!!

ምን አይነት ምጣት ነው፣ ባንች ላይ የመጣ
ቅጥረኛና ከሀዲው፣ ዙፋን ላይ ሲወጣ
ባላገር ተሚጋች፣ ባልሰራው ሲቀጣ
በኢሕአዴግ ድራማ፣ መላቅጡን ባጣ
ዘራፍ በል አበሻ፣ አምርረህ ተቆጣ
አገር ከጂው ንጉሥ፣ ተፈንቅሎ ይውጣ!

እንዲህ ያለ መንግሥት፣ የመንግሥት ፈጣጣ
አታላይ ቀጣፊ፣ ነውረኛ ዓይን አውጣ
ውሸትን አንግሦ፣ እውነትን የቀጣ
አንድነትን ገሎ፣ ጥላቻን ያመጣ
ሠላምን ገፍትሮ፣ ጦርነት የቃጣ
አገር ከሀዲ ማን ነው፣ ቅጥረኛ ቢሏችሁ
መለስ ነው፣ መለስ ነው፣ መለስ ነው፣ ካላችሁ
መልሱ ትክክል ነው፣ ስህተት የለባችሁ።